# ጋና ኮራሁብሽ!! እኛስ ምን እንማራለን?

“እኔ በጋና ሰምሮ ማየት የምፈልገው የሕግ የበላይነት፣ ፍትሐዊ የፍርድ ሒደትና፣ አንድነታችን ተጠናክሮ የምንኖርባት ሐገር ነው።”

ጆን አታሚልስ የጋና የወቅቱ ፕሬዚዳንት።

አዎን ዛሬ ጋና ታላቋ የዲሞክራሲ ምሳሌ መሆኗን በሐገሪቷ ከተደረጉት ምርጫ ሌላ ሰሞኑን ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በአክራ ጉብኝታቸው ባደረጉት ንግግር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ጋና ለምን ለዚህ ተመረጠች ለሚለው ጥያቄ ጥሩ የሚያጠግብ መልስ ሰጥተውናል። ጋና ዛሬ በምርጫ፣ የሕዝቦቿን ሰብዓዊ መብት በማክበር፣ በማደግና በማበብ ላይ በሚገኙ የሙያ ማህበራት መጠናከር ባላት የአዎንታ ፍላጎት ሰላማዊና የሕዝብ ተሳትፎ ያለበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስራች ሐገር ሆናለች።

እናስ የኛዎቹ መሪዎች ከጋና ምን ይማራሉ? ምርጫ 97 እንከንየለሽ ይሆናል ተብሎ ዓለም ሁሉ በታዛቢነት እውን ይሆን እንዴ በማለት ሲጠባበቁ፣ በምትኩ የታየው ግን በዲሞክራሲ ካባ ተሸፍኖ የነበረው የአቶ መለስና ግብረአበሮቹ ትክክለኛ አውሬ መልካቸው ፈጠ የወጣበትና ማንነታቸውን ያሳዩበት ነበር። (እንከንየለሽስ የጋናው ምርጫ፣ ኮሽታ ጫጫታ የሌለበት፣ ተሸናፊው መሸነፉን አምኖ በፀጋ ተቀብሎ ሥልጣኑን ያስረከበበት)

በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ሕዝብና በአለም አቀፉ ሕብረተሰብ ጥሩ ተቀባይነት እናገኛለን እንዲሁም ደግሞ በሌላ በኩል ጠንካራ ተቃዋሚም ስለሌለ ድሉ የኛ እንጂ የማንም አይሆንም በሚል ዝቅ ያለ አስተሳሰብ በመመካት ተነሳስተው ስለነበር እውነቱ ግን እነሱ ያሰቡት ሳይሆን በተቃራኒው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመሩኛል ያላቸውን መሪዎቹን መረጠ፣ ድምፁን በከፍተኛ ቁጥር በመውጣት ሰጠ። ነገር ግን ይሰጠኝ ባለው ዲሞክራሲ ምትክ ጥይት ተሰጠው፡ ወጣት፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ፣ ወንድ፣ ሴት ሳይል የጥይት ሰለባ ሆኑ። በሐገሪቱ ላይ ሊገነባ የነበረው ዲሞክራሲ በአንድ ጊዜ ተናደ። የሚገርመው ግን መንግስት ተብዬው እራሱ በአንድ ጀምበር የናደውን ዲሞክራሲ በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንዲሉ እውነተኛ ለሕዝብ የቆሙትን እና ለሕዝብ ድምፅ መከበር እንታገላለን ያሉትን የሕዝብ ተመራጮች እና የዲሞክራሲ ታጋዮች ሕገመንግሥት በመናድና በዘር ማጥፋት ወንጀል በመክሰስ መንግስት ራሱ ከሕግ በላይና ፈላጭ ቆራጭ በሆነበት በካንጋሮ ፍርድቤቱ ለይስሙላ በየጊዜው በማመላለስ ይጫወት የነበረው ድራማ የቅርብ የማይረሳ ትዝታችን ነው።

አሁንማ ጭራሽ የፖለቲካው ምህዳሩ በጣም የጠበበ ተቃዋሚዎች መንቀሳቀስና በሕገመንግሥቱ ደንብ መሠረት እንኳን ሕዝቡን እነዳያስተባብሩ በጣም ከፍተኛ ወከባ የበዛበት እንደሆነ ዘወትር የምንሰማው ነው። በ2002 ምርጫ ኢሕአዴግ ሜዳውን ለብቻው ይዞ እራሱ አጥቂ እራሱ ተከላካይ እራሱ ግብ አስቆጣሪ እራሱ አሸናፊ ለመሆን ዝግጅቱን በሰፊው ተያይዞታል። እውነትም ዲሞክራሲ!! ከጋና ጋር ስናስተያየው የኛው ድራማ ነው እንጂ ምርጫ የሚለው ቃል ማታለያ ነው። ከምርጫ 97 መጪውን ምርጫ (ምርጫ ከተባለ) ልዩ የሚያደርገው ወያኔ በመጪው ምርጫ ኮሮጆ መስረቅ አያስፈልገውም።ከምርጫው ቀን በፊትም አሸነፍኩ ብሎ ማወጅ ይችላል።

ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ዛሬ አፍሪቃ ከላይ በተጠቀሱት አይነት የእኔ ብቻ ልግዛ ማንም ስልጣኔን ከእኔ መውሰድ አይገባውም በሚል አስተሳሰብ በትምክህት በተወጠሩ፣ የሕዝብ በድህነት መኖር፣ በረሃብ በችጋር በበሽታና በመሳሰሉት ማለቅ ምንም የማይሰማቸው፣ እነሱና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ደጋፊዎቻቸው ብቻ ተንደላቀው እየበሉ እየጠጡና እየጨፈሩ መኖር በሚፈልጉ አይነት መሪዎች የተሞላች አህጉር መሆኗን አለም በሙሉ ያወቀው ነው።

የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብትን በተመለከተ ሲሆን አነገታቸውን የሚደፉት የአፍሪቃ መሪዎች ገንዘብና እርዳታ ለመጠየቅ ግን አፍጠው ሲመጡ እፍረት እንኳን አይታይባቸውም። በዚህም የኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ጥሩ ልምድ እንዳላቸው በመታወቁ ሀብታሞቹ ሐገራት በሚያደርጉት ስብሰባዎች ላይ የልመና አቁፋዳቸውን ይዘው መገኘት የተለመደ ስራቸው ሆኗል። አንድ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመላላክ ትምህርት ዲግሪ አገኙ ሲባል ሰምቼ ነበር፣ የተመረቁበት ትምህርት ልመናንም ያካትት ነበር እንዴ እንዲህ የተዋጣላቸው ለማኝ የሆኑት? ወይንስ ሐገራችን ከ1970ዎቹ በኋላ በረሃብና በችግር እየታወቀች በመምጣትዋ በኛ ስምና በኛ መሪ መለመኑ አያሳጣም ተብሎ ተገምቶ ነው? ግን እኮ ደግሞ የተለመነው ገነዘብም በድሃውና በተራበው ሕዝብ ስም ይለመን እንጂ ለተረጂው ከሚደርሰው ይልቅ በተለያዩ መንገዶች በመጠቀም ወደኪሳቸው የሚገባው መጠኑ እጅግ ከፍ ያለ ቁጥር ድርሷል። ለዚህም በቅርቡ አንድ በዩናየትድ ኪንግደም የሚታተም ኢንዲፔንደንት የተባለ ጋዜጣ የኛን መሪዎች በተመለከተ ያወጣው ፅሁፍ ቀልብ የሳበ ነበር (ለማነበብ ይጫኑ http://www.ethiomedia.com/carepress/meles_zenawi_money_laundering.html ). በዚህ አይነት እንግዲህ አሰቡት በሙስና የተዘፈቁት የአፍሪካ መሪዎች የእያንዳንዳቸው የባንክ ንብረት ገሃድ ቢወጣ የሚኖራቸው የገነዘብ መጠን የትዬለሌ እንደሚሆን አትጠራጠሩ። ሌላው በጣም የሚገርመው ግን ከእነዚሁ ለጋሽ ከሚባሉት ሐገራት ዩናይትድ ኪንግደም አንዷ ስትሆን ወደ ሐገሯ ባንክ እየተመለሰ ተቀማጭ የሚሆነውን ገንዘብ ሳታውቅ ቀርታ ነው ጥያቄ እንኳን የማታቀርበው? ወይንስ የብሪታኒያ መንግስት ሌላ ያሰበው ነገር አለ?

ጋና ዛሬ ከዚህ ሁሉ ግብስብስ የአፍሪቃ መሪዎች ከላቸው መጥፎ ስም እራስዋን እያወጣች ነው። ከደሙ ነፃ ነኝ በማለት እጅዋን እየታጠበች ነው፡ የዛሬ 30 አመት ገደማ በአፍሪቃውያን ዘንድ እስካሁንም እነደ ባሕል በሚቆጠረው መንግሥትን በመፈንቅለ መንግሥትና በሐይል አሰገድዶ ሥልጣን በሚያዝባት አፍሪቃ ተሳታፊ የሆነችው ጋና፣ ዛሬ እራሷን ከታላላቆቹ የሰውን መብት ከሚያከብሩት አገሮች ጋር እራሷን በማስተካከሏ ይኸው የመሪዎቿን ድካምና ፍሬ ለአለም እያሳየች ነው።

አንዳንድ ደካሞች ለአፍሪካውያን ዲሞክራሲ አይገባቸውም (don’t understand) እናም አይገባቸውም ሲሉ ይደመጣል። ግን ማንም ማወቅ ያለበት ዲሞክራሲ ስንወለድ አብሮን የተሰጠን ፀጋ እንጂ ማንም እየለካ እና እየሰፈረ እንደ ቁመታችንና እንደ ክብደታችን የሚያድለን አይደለም። እኛም ደግሞ መብታችንን በአግባቡና በሥርዓቱ መጠቀም ማንም ከሕግ በታች እንጂ ከሕግ በላይ መሆን እንደማንችል አውቀን እርስ በርሳችን በመከባበር የምንኖር ከሆነ፣ አነድነታችን የጠነከረ ሰላም በመካከላችን ይሰፍንና በዛው መጠንም እያደግን ያሉብንን ችግሮች እየፈታን የምንሔድ ጥሩ ዜጎች ልንሆን እንበቃለን።

ፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ ለምርጫ በሚወዳደሩበት ወቅት ሁሉንም እየጣሉና እያሸነፉ ሲመጡ የዓለምን ትኩረት የሳበ ትልቅ አጀንዳ ሆነ። በዚያን ወቅት ብዙዎች ዋይት ሐውስም ከመግባት የማይመለሱ መሆናቸውን ሲያውቁ በጥቁሮች እና በነጮች ካምፕ ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆነ። አንዳንዶች ይሄ ዲሞክራሲ አለ ለማስባል እና ለማስመሰል ነው እንጂ አንድን ጥቁር ፈቅደው ዋይት ሐውስ አያስገቡም እነደምንም ብለው እንዲሸነፉ ያደርጓቸዋል ሲባል ተሰማ በዙዎቻችንም ያንን ቀኝት ተቀብለን ያቀነቀንን ነበርን፣ ብዙዎችም ተስፋ ሳይቆርጡ ከሳቸው ጋር ተጉዘው እውነትም ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ሙሉ ዲሞክራሲ የሰፈነባት አገር መሆኗንና ተስፋ ባለመቁረጥ ካለሙትና ከሰቡት ለመድረስ **“ይቻላል”** ብለው ፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ አሳይተውናል። ዛሬም ለአፍሪካ ሁሉ ለገር ይቻላታል ብለው ያስደምጡናል። አፍሪካ ሁሉ ነገር አላት ያልተነካ ሃብት ጉልበት ሁሉ ነገር አላት፣ ለሕዝብ የሚያስብ ለሕዝብ የሚሰራ ያለውን ገንዘብ በሙሉ ወደ ኪሱ ሳይሆን ለሥራ የሚያውል መሪ ካላት፣ የሕዝቦችን ሰብዓዊ መብት የሚያከብርና እራሱ ለሕግ ተገዝቶ ሕግን የሚያስከብር መሪ ካላት አፍሪካ የማታድግበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ጋና በዚህ አርአያነቷን አሳይታለች፣ ለዚህም ሽልማቷ ትውልደ አፍሪካ የሆኑትንና አፍሪካን የሚያኮሩትን ባራክ ኦባማን በከፍተኛ ድምቀት ተቀብላ አስተናግዳለች። ለዚህም የጋና መንግስትና ሕዝብ ከፍተኛ ኩራት ሊሰማው ይገባል ተሰምቶታልም። የኛውም ጠቅላይ ሚኒስትር ጊዜው የረፈደ አይመስለኝም አሁንም ለሕዝብና ለሐገር ጥሩ ሰርቶ ለታሪክ የሚወሳ ጥሩ ስም ማስቀረት ይቻላል። የእኛም መሪዎች ተብዬዎች (የወደፊቶቹም) ከዚህ ተምረው ለሐገር የሚበጅ እና እነሱንም ታሪክ በመልካም ሥራቸው የምታነሳቸው ይሆኑ ዘንድ ቀና አእምሮ እንዲያድላቸው እስቲ ሁላችንም ብድግ ብለን አቡነዘበሰማያት እንበል

ፍቅርና ሠላም ያድለን

ፍቅሩ ይበልጣል ነኝ ከዩኬ